የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፹፭
አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No. 85
ADDIS ABABA 31st August ,2017

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፬፻፲፫/፪ሺ፱ ዓ.ም
የኢትዮጵያ ማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፊዩል ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ ደንብ (ማሻሻያ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………………ገጽ ፱ሺ፰፻፺፰

**CONTENT**

Regulation No. 413/2017
Ethiopian Mineral, Petroleum and Bio-Fuel Establishment Council of Ministers Regulation (Amendment) Regulation ………………….page 9898

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፲፫/፪ሺ፱

## የኢትዮጵያ ማዕድን፣ ነዳጅ እና ባዮፊዩል ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ ደንብን ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፯ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፭ እና ፴ (፯) እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፳፩ እና ፵፯ (፩)(መ) መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ " የኢትዮጵያ ማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፊዩል ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ ደንብ (ማሻሻያ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፲፫/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ማሻሻያ

የኢትዮጵያ ማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፊዩል ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፷፯/፪ሺ፯ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩/ በደንቡ ከአንቀጽ ፮ (፲፩) በኋላ የሚከተለው አዲስ

Council of Ministers Regulation No. 413/2017

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO AMEND THE ETHIOPIAN MNINERAL, PETROLEUM AND BIO-FUEL CORPORATION REGULATION

This regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and 30 (7) of Definition of Power and duties of the Executive organs of Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015 (as amended) and Article 21, and 47 (1)(d) of Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Mineral, Petroleum and Bio-Fuel Establishment Council of Ministers Regulation (Amendment) Regulation No. 413/2017".

### 2. Amendment

The Ethiopian Mineral, Petroleum and Bio-Fuel Corporation Establishment Council of Ministers Regulation No. 367/2015 hereby amended as follows:

1/ The following new sub-article (12) is added after sub-article (11) of Article 6 of the Regulation:

ንዑስ አንቀጽ (፲፪) ተጨምሯል፦

"፲፪/ በግል ኩባንያዎች አማካይነት በሚካሄዱ የነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ እንዲሁም በማዕድን ልማት ሥራዎች ውስጥ የመንግሥትን ድርሻ በመወከል መሳተፍና ማስተዳደር፡፡

፪/ የደንቡ አንቀጽ ፯ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፯ ተተክቷል፦

"፯. **ካፒታል**

ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፩ ቢሊዮን ፮፻፸፰ ሚሊዮን ፮፻፵ ሺ (አንድ ቢሊዮን ስድስት መቶ ሰባ ስምንት ሚሊዮን ስድስት መቶ አርባ ሺ) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፬፻፲፱ ሚሊዮን ፮፻፷ ሺ(አራት መቶ አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ስድስት መቶ ስልሳ ሺ) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡"

፫. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

**ኃይለማርያም ደሣለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

"12/ to represent the Government in its equity participation and administration of private companies engaged in petroleum and natural gas as well as minerals development;"

2/ Article 7 of the Regulation is deleted and replaced by the following new Article 7:

"7. **Capital**

The authorized capital of the corporation is Birr 1,678,640,000.00 (One Billion, Six Hundred Seventy Eight Million, Six Hundred Forty Thousand) of which Birr 419,660,000.00 (Four Hundred Nineteen Million Six Hundred Sixty Thousand) is paid up in cash and in kind."

3. **Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 31st day of August, 2017**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me